ቀን:- ____________________

# የውክልና ስልጣን ማስረጃ

ወካይ:- ____________________________

አድራሻ:- ____________________________

____________________________

ተወካይ :- ____________________________

አድራሻ:- ____________________________

____________________________

እኔ ወካይ ለተወካይ የምሰጣቸው የውክልና ስልጣን ተወካይ እንደ እኔ በመሆን በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘውን ማንኛውም የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረቴን እንዲጠብቁ ፣ እንዲቆጣጠሩ ፣ እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲሸጡ፣ እንዲለውጡ፣ እንዲያከራዩ፣ እንዲያኮናትሩ፣ የኪራይም ሆነ የኮንትራት ገንዘብ ተሳስበው እንዲቀበሉ፣ ውል እንዲያፈርሱ፤ በስሜ እኔ የተዋዋልኳቸውን የኪራይም ሆነ ማንኛውም አይነት ውሎች ተወካይ እንዲያድሱ ማፍረስ እንዲችሉ፣ በስሜ ሰነድ ላይ እንዲፈርሙ፣ ሰነድ መስጠትም ሆነ መቀበል እንዲችሉ፣ ገንዘብ ፈርመው እንዲቀበሉ፣ በስሜ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲገዙ፤ ስሙን በስሜ እንዲያዞሩ፤ በስሜ አክሲዮን እንዲያቋቁሙ፣ በስብሰባዎች ላይ እንዲገኙ፣ ድምፅ እንዲሰጡ፣ የውሳኔ ሃሳብን እንዲቀበሉ፣ እንዲያፀድቁ፣ የአክስዮን ድርሻዬን እንዲረከቡ፣ ሌሎች አክስዮኖች እንዲገዙ፣ እንዲሁም ኮንደምንየምና ቤት እንዲገዙልኝ፣ እንዲረከቡልኝ፣ እንዲያስተዳድሩ፣ ገንዘብ ፈርመው እንዲቀበሉ፣ አስፈላጊ የሆኑ ማንኛውንም ክፍያዎችን እንዲከፍሉ፣ ግብር እንዲገብሩ፣ የኢንቨስትመንት ፍቃድ እንዲያወጡ፣ የንግድ ፈቃድ እንዲያወጡ፣ በስሜ የግንባታና የእድሳት ፈቃድ እንዲያወጡ፣ ለግንባታ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎችንም ሆነ ሲሚንቶ እንዲገዙ፣ የግንባታ ስራ እንዲያካሂዱ፣ ካርታ እንዲያወጡ፣ በኢትዮቴሌኮም በውሃና ፍሳሽ አገልግሎት፣ በኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እየቀረቡ፣ በስሜ ውል ተዋውለው ውሃ መብራት ስልክ እንዲያስገቡ፣ ውሃ ፣ መብራት፣ ስልክ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ ፣መንጃ ፍቃድ እንዲያሳድሱ፣ ሊብሬ እንዲያወጡ፣ ሲም ካርድ እንዲያወጡ፣ ሲም ካርድ ቢጠፋ እንዲያዘጉና እንዲያስከፍቱ፣ በስሜ በማንኛውም ባንክ ተመዝግቦ የሚገኘውን የባንክ አካውንቴን እንዲያንቀሳቅሱ፣ ገንዘብ ገቢና ወጪ እንዲያደርጉ፣ በስሜ ቼክ ፈርመው መስጠትም ሆነ መቀበል እንዲችሉ፣ ቼክ እንዲመነዝሩ፣ በውርስም ሆነ በስጦታ የሚደርሰኝን ድርሻ ንብረት ወደ ስሜ እንዲያዛውሩ፣ በውርስ የሚደርሰኝን ገንዘብ ድርሻዮን ሰነድ ላይ ፈርመው እንዲቀበሉ በስሜ የሚሰጠኝን የካሳ ክፍያ አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አማልተው እንዲቀበሉ፣ በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘውን የሚንቀሣቀስም ሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት በዋስትና በማስያዝ ወይም ያለ ዋስትና ገንዘብ ከማንኛውም የመንግስትም ሆነ የግል ባንኮች፣ ከአበዳሪ ድርጅት እንዲሁም ከግለሰብ በስሜም ሆነ በስማቸው እንዲበደሩ እና እንዲያበድሩ ተሳስበው እንዲከፍሉና እንዲቀበሉ ገንዘብና ሰነድ ፈርመው እንዲቀበሉ ሰነድ እንዲሰጡ በስሜ ማንኛውም ክፍያዎችን እንዲከፍሉ፣ ከማንኛውም ተቋም የትምህርት የልደት የምስክር ወረቀት ያላገባ ስለመሆኔ ማስረጃዎችን እንዲያወጡ ማረጋገጫ እንዲያስመቱ መልቀቂያና ክሊራንስ መሸኛ እንዲያወጡ በአጠቃላይ በመንግስታዊ መ/ቤትም ሆነ ህዝባዊያን ድርጅቶች አስተዳደር መ/ቤት በአገር ውስጥ ገቢ፣ በክ/ከተማ በቀበሌ፣ ወረዳ ከተማ ልማት፣ በመሬት አስተዳደር በመንገድ ትራንስፖርት፣ በጤና ቢሮ፣ በኤምባሲ፣ በኢሚግሬሽን፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በኪራይ ቤቶች፣ በቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት፣ በፖስታ ቤት፣ በንግድና ኢንዱስትሪ፣ በማዘጋጃ ቤት፣ በኢንቨስትመንት ቢሮ፣ በከተማ ልማት፤ ትምህርት ሚኒስቴር፣ በፍ/ቤት እየቀረቡ ያለኝን ጉዳይ ሁሉ ተከታትለው እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ፤ በማንኛውም ቦታዎች ላይ እንደ እኔ ተጠሪ እንዲሆኑ፣ በስሜም ሆነ በንብረቴ ላይ ክስ ክርክር ቢነሣ የሕግ ጠበቃ ወክለው በማንኛውም ፍ/ቤት በመቅረብ እንዲከራከሩ መልስ እንዲሰጡ ቃለ መሀላ እንዲያቀርቡ አፈፃፀም እንዲከታተሉ ማረጋገጫ እንዲፈርሙ ይግባኝ እንዲጠይቁ ውሳኔ እንዲቀበሉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ውክልና መስጠትም ሆነ መሻር እንዲችሉ ይህንን ሙሉ የውክልና ሥልጣን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ 58/ሀ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2199/2205 መሠረት መስጠቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የወካይ ሙሉ ስምና ፊርማ

____________________________

ቀን ________________________

## <u>የውክልና ስልጣን ማስረጃ</u>

1. ወካይ:- ____________________________
   አድራሻ:- ____________________________
   ____________________________

2. ወካይ:- ____________________________
   አድራሻ:- ____________________________
   ____________________________

ተወካይ:- ____________________________
አድራሻ:- ____________________________
____________________________

እኛ ወካይ ለተወካይ የምሰጣቸው የውክልና ስልጣን ተወካይ እንደ እኛ በመሆን በስማችን ተመዝግቦ የሚገኘውን ማንኛውም የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረታችንን እንዲጠብቁ፣ እንዲቆጣጠሩ፣ እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲሸጡ፣ እንዲለውጡ፣ እንዲያከራዩ፣ እንዲያኮናትሩ፣ የኪራይም ሆነ የኮንትራት ገንዘብ ተሳስበው እንዲቀበሉ፣ ውል እንዲያፈርሱ፤ በስማችን እኛ የተዋዋልናቸውን የኪራይም ሆነ ማንኛውም አይነት ውሎች ተወካይ እንዲያድሱ ማፍረስ እንዲችሉ፣ በስማችን ሰነድ ላይ እንዲፈርሙ፣ ሰነድ መስጠትም ሆነ መቀበል እንዲችሉ፣ ገንዘብ ፈርመው እንዲቀበሉ፣ በስማችን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲገዙ፤ ስሙን በስማችን እንዲያዞሩ፤ በስማችን አክሲዮን እንዲያቋቁሙ፣ በስብሰባዎች ላይ እንዲገኙ፣ ድምፅ እንዲሰጡ፣ የውሳኔ ሃሳብን እንዲቀበሉ፣ እንዲያፀድቁ፣ የአክስዮን ድርሻችንን እንዲረከቡ፣ ሌሎች አክስዮኖች እንዲገዙ፣ እንዲሁም ኮንደምንየምና ቤት እንዲገዙ፣ እንዲረከቡ፣ እንዲያስተዳድሩ፣ ገንዘብ ፈርመው እንዲቀበሉ፣ አስፈላጊ የሆኑ ማንኛውንም ክፍያዎችን እንዲከፍሉ፣ ግብር እንዲገብሩ፣ የኢንቨስትመንት ፍቃድ እንዲያወጡ፣ የንግድ ፈቃድ እንዲያወጡ፣ በስማችን የግንባታና የእድሳት ፈቃድ እንዲያወጡ፣ ለግንባታ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎችንም ሆነ ሲሚንቶ እንዲገዙ፣ የግንባታ ስራ እንዲያካሂዱ፣ ካርታ እንዲያወጡ፣ በኢትዮቴሌኮም በውሃና ፍሳሽ አገልግሎት፣ በኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እየቀረቡ፣ በስማችን ውል ተዋውለው ውሃ መብራት ስልክ እንዲያስገቡ፣ ውሃ ፣ መብራት፣ ስልክ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ ፣መንጃ ፍቃድ እንዲያሳድሱ፣ ሊብሬ እንዲያወጡ፣ ሲም ካርድ እንዲያወጡ፣ ሲም ካርድ ቢጠፋ እንዲያዘጉና እንዲያስከፍቱ፣ በስማችን በማንኛውም ባንክ ተመዝግቦ የሚገኘውን የባንክ አካውንታችንን እንዲያንቀሳቅሱ፣ ገንዘብ ገቢና ወጪ እንዲያደርጉ፣ በስማችን ቼክ ፈርመው መስጠትም ሆነ መቀበል እንዲችሉ፣ ቼክ እንዲመነዝሩ፣ በውርስም ሆነ በስጦታ የሚደርሰንን ድርሻ ንብረት ወደ ስማችን እንዲያዛውሩ፣ በውርስ የሚደርሰኝን ገንዘብ ድርሻችንን ሰነድ ላይ ፈርመው እንዲቀበሉ በስማችን የሚሰጠኝን የካሳ ክፍያ አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አማልተው እንዲቀበሉ፣ በስማችን ተመዝግቦ የሚገኘውን የሚንቀሣቀስም ሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት በዋስትና በማስያዝ ወይም ያለ ዋስትና ገንዘብ ከማንኛውም የመንግስትም ሆነ የግል ባንኮች፣ ከአበዳሪ ድርጅት እንዲሁም ከግለሰብ በስማችንም ሆነ በስማቸው እንዲበደሩ እና እንዲያበድሩ ተሳስበው እንዲከፍሉና እንዲቀበሉ ገንዘብና ሰነድ ፈርመው እንዲቀበሉ ሰነድ እንዲሰጡ በስማችን ማንኛውም ክፍያዎችን እንዲከፍሉ፣ ከማንኛውም ተቋም የትምህርት የልደት የምስክር ወረቀት ያላገባ ስለመሆናችን ማስረጃዎችን እንዲያወጡ ማረጋገጫ እንዲያስሙቱ መልቀቂያና ክሊራንስ መሸኛ እንዲያወጡ በአጠቃላይ በመንግስታዊ መ/ቤትም ሆነ ህዝባዊያን ድርጅቶች አስተዳደር መ/ቤት በአገር ውስጥ ገቢ፣ በክ/ከተማ በቀበሌ፣ ወረዳ ከተማ ልማት፣ በመሬት አስተዳደር በመንገድ ትራንስፖርት፣ በጤና ቢሮ፣ በኤምባሲ፣ በኢሚግሬሽን፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በኪራይ ቤቶች፣ በቤቶች ልማት ኘሮጀክት ጽ/ቤት፣ በፖስታ ቤት፣ በንግድና ኢንዱስትሪ፣ በማዘጋጃ ቤት፣ በኢንቨስትመንት ቢሮ፣ በከተማ ልማት፤ ትምህርት ሚኒስቴር፣ በፍ/ቤት እየቀረቡ ያለንን ጉዳይ ሁሉ ተከታትለው እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ፤ በማንኛውም ቦታዎች ላይ እንደ እኛ ተጠሪ እንዲሆኑ፣ በስማችንም ሆነ በንብረታችን ላይ ክስ ክርክር ቢነሣ የሕግ ጠበቃ ወክለው በማንኛውም ፍ/ቤት በመቅረብ እንዲከራከሩ መልስ እንዲሰጡ ቃለ መሀላ እንዲያቀርቡ አፈፃፀም እንዲከታተሉ ማረጋገጫ እንዲፈርሙ ይግባኝ እንዲጠይቁ ውሳኔ እንዲቀበሉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ውክልና መስጠትም ሆነ መሻር እንዲችሉ ይህንን ሙሉ የውክልና ሥልጣን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ 58/ሀ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2199/2205 መሠረት መስጠታችንን በፊርማችን እናረጋግጣለን፡፡

የወካዮች ሙሉ ስምና ፊርማ

1 ________________________

2 ________________________